# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጂኦግራፊ ታሪካዊ ጥናት ምርመራ ሦስተኛው ክፍል ነው። መጽሐፉ ሐዋርያት ለወንጌል ስብከት የተዘዋወሩባቸውን አገሮች፣ ቀበሌዎችና ከተሞች፤ እንዲሁም ከወንጌል ስብከት ጉዞአቸው ጋር ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ስፍራ ይገልጻል። በተጨማሪም በዮሐንስ ራእይ ስለ ተጠቀሱት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ያስረዳል።

ታሪኩን ከነስፍራው ለመረዳት የሚያስችሉ ካርታዎች ስለሚገኙ አንባቢው መጽሐፉን በቀላሉ ለመከታተል ይችላል።

# ማስገንዘቢያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ዘመናት እንደ አውሮፓ አቈጣጠር ናቸው።

# የወንጌል መስፋፋት

በዚህ ክፍል በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ ፰—፲፪ የተገለጸውን እናገኛለን ። ይህ ክፍለ ጊዜ ከእስጢፋኖስ ሞት (፴፯ ዓ. ም.) እስከ መጀመሪያው የጳውሎስ የወንጌል ስብከት ጉዞ (፵፭ ዓ. ም.) ነው ። በዚህ ክፍለ ጊዜ ሐዋርያት የጐበኙአቸውን ቦታዎችና በየእንዳንዱም ቦታ የፈጸሙትን አገልግሎት እንገልጻለን ።

**1. በዚህ ክፍለ ጊዜ ዋንኞቹ ከተሞች የሚከተሉት ነበሩ ፦**

ሀ) ኢየሩሳሌም ፦የፍልስጥኤም ዋና ከተማና የአይሁድ ማምለኪያ መከከላዊ ከተማ ነበረች ። (ሁለተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጂአግራፊ ተመልከት ።)

ለ) ሰማርያ ፦ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን የሚገኝ የአሥሩ ነገዶች ጥንታዊ ዋና ከተማ ነበር ። በዚህ ከተማ ፊሊጶስ ስለ ወንጌል ሰብኮአል ። (የሐዋ. ፰ ፥ ፭—፳፭)

ሐ) ቂሣርያ ፦(የሐዋ. ፲ ፥ ፩—፵፰) ፦ሮማውያን ፍልስጥኤምን ከያዙ በኋላ የዚህ ክፍል ግዛታቸው ዋና ከተማ አደረጉት ። ይህ ከተማ የተመሠረተው በባሕር ጠረፍ ላይ ነበር ። እዚህ ቆርኔሌዎስ በክርስቶስ አመነ ።

መ) ኢዮጴ ፦የፍልስጥኤም ዋንኛው የባሕር በር ነበር ። ሞታ የነበረችው ጣቢታ (ዶርቃ የተባለችው) ነፍስ የዘራችው እዚህ ነበር ። (የሐዋ. ፲፩ ፥ ፲፱—፴) ። የሚገኘውም በሰሜናዊ ሶርያ ማለት በቶሩስና በሊባኖስ ተራሮች መከከል ነበር ።

ሰ) ጠርሴስ ፦የሐዋርያው ጳውሎስ የትውልድ አገርና የኪልቅያ አውራጃ ዋና ከተማ ነበር ። (የሐዋ. ፳፩ ፥ ፴፱)

**2. በዚህ ክፍለ ጊዜ የተፈጸሙት ዋና ዋና ክንውኖች እንደሚከተለው ነበሩ ፦**


ሀ) የፊሊጶስ ጉዞ ፦(የሐዋ. ፰ ፥ ፭—፵) ። ፊሊጶስ ከተመረጡት ሰባት ሰዎች አንዱ ነበር (የሐዋ. ፮ ፥ ፫—፭) ። በስደት ምክንያት ወደ ሰማርያ ሄደና እዚያ ወንጌልን አስተማረ ። ቀጥሎም ወደ ጋዛ ወርዶ (የሐዋ. ፰ ፥ ፳፮) ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ወደ ክርስቶስ መለሰ ። በየከተማውም ወንጌልን እያስተማረ ወደ ቂሣርያ ሄደ ። (የሐዋ. ፰ ፥ ፵)

ለ) የጳውሎስ ጉዞ ፦(የሐዋ. ፱ ፥ ፩—፴)

1. ወደ ደማስቆ ሲሄድ በመንገድ ላይ ክርስቶስን ተቀበለ ።

2. ከደማስቆ ወደ ዓረብ አገር ሄደና (ገላ. ፩ ፥ ፲፯) በኋላም ወደ ደማስቆ ተመለሰ ።

3. ሌሎች ደቀ መዛሙርት በቅጥር ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱትና ከደማስቆ አምልጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። በኢየሩሳሌም በበርናባስ አማካይነት ከሐዋርያት




ዋና ዋና ከተሞችና አውራጃዎች ።

ጋር ተዋወቀ። ከዚህም በኋላ ወደ ቂሣርያ ሄደ ፤ ከዚያም ወደ ጠርሴስ ተጓዘ። (የሐዋ. ፱ ፣ ፳፮—፴)

ሐ) <u>የጴጥሮስ ጉዞ</u>፡—(የሐዋ. ፱ ፣ ፴፪—፲፩ ፣ ፲፰)

1. ወደ ልዳ ሄደ። እዚያም በነበረበት ጊዜ አንድ ሰው ፈወሰ። (የሐዋ. ፱ ፣ ፴፪—፴፭)

2. ከልዳም ተነሥቶ ወደ ተጠራበት ወደ ኢዮጴ ሄደና ጣቢታን (ዶርቃ የተባለ ችውን) ከሞት አስነሣ። (የሐዋ. ፱ ፣ ፴፮—፵፫)

3. ከዚያም ቆርኔሌዎስ ጠራውና ወደ ቂሣርያ ሄደ። (የሐዋ. ምዕራፍ ፲)

4. በኋላም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። (የሐዋ. ፲፩ ፣ ፩—፲፰)

መ) <u>የበርናባስ ጉዞ</u>፡—(የሐዋ. ፲፩ ፣ ፲፱—፴)። በሶርያው አንጾኪያ አንድ ጽኑ ቤተ ክርስቲያን ተቋቁሞ ነበር። በዚህ ቦታ ነበር አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ "ክርስቲያን" የተባሉት። እነዚህ ክርስቲያኖች ሰባኪያንን ወደ አረማውያን በመላክ የመጀመሪያዎቹ ነበሩ። ይህ ወሬ በኢየሩሳሌም እንደ ተሰማ ወደ እዚሁ ወደ አንጾኪያ ከተማ በርናባስ ተላከ። በኋላም ወደ ጠርሴስ ሄዶ ጳውሎስን ተገናኘና በአንጾኪያ የነበረውን ሥራ እንዲያግዘው ወደ አንጾኪያ ይዞት ተመለሰ።

ሠ) <u>የበርናባስና የጳውሎስ ጉዞ</u>፡—(የሐዋ. ፲፩ ፣ ፳፭—፴ ፤ ፲፪ ፣ ፳፭)

1. ሁለቱም ከጠርሴስ ወደ አንጾኪያ መጡ። እዚህ አብረው አንድ ዓመት ሠሩ።

2. ቀጥሎም የአንጾኪያ አማኞች በይሁዳ ለነበሩት ወንድሞች የላኩትን ስጦታ ይዘው ወደ ይሁዳ ሄዱ።


3. በኋላም ወደ አንጾኪያ ተመለሱ።

## <u>የጳውሎስ ጉዞዎች</u>

በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ ፲፫ እስከ ፳፰ የተነገረው በ፳ ዓመታት ውስጥ የሆነ ነበር። በዚህ ክፍለ ጊዜ ጳውሎስ በወንጌል መልእክተኛነት ሦስት ፣ በእስረኛነት አንድ ጉዞዎች አድርጓአል። በእነዚህ ጉዞዎች የጐበኛቸው ስፍራዎች በየአንዳንዱ ስፍራ ከፈጸመው ተግባር ጋር ተገልጸዋል።

## ፩፤ የትንሹ እስያ አውራጃዎች

ሀ) <u>የጥቁር ባሕር አካባቢ አውራጃዎች</u>


ጥቁር ባሕር
ኢጣልያ
መቄዶንያ
ቢታንያ
ገላትያ
ጳንጦስ
ሚስያ
የኤጂያን ባሕር
ግሪክ አገር
ፍርግያ
ሉድ
ቀጰዶቅያ
ሊቃኦንያ
ጲስድያ
ኪልቅያ
ሉቅያ
ቀርጤስ
ቆጵሮስ
ታላቁ ባሕር
የትንሹ እስያ
አውራጃዎች
ግብፅ

1. ጳንጦስ (የሐዋ. ፪ ፥ ፱ ፤ ፲፰ ፥ ፪ ፤ ፩ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፩) ። አቂላ የተባለው የጳውሎስ ረዳት አገሩ እዚህ ነበር ።

2. ቢታንያ (የሐዋ. ፲፮ ፥ ፯ ፤ ፩ ጴጥሮስ ፩ ፥ ፩)

ለ) <u>የኤጂያን ባሕር አከባቢ አውራጃዎች</u>

1. ሚስያ ከሉድ በስተ ሰሜን ይገኝ ነበር (የሐዋ. ፲፮ ፥ ፯ ና ፰) ። ጢሮአዳ በዚህ አውራጃ የሚገኝ ከተማ ነበር ።

2. ሉድ ከሚስያ በስተ ደቡብና ከፍርግያ በስተ ምዕራብ ይገኝ ነበር ። ዋና ከተማው ኤፌሶን ነበር ።

ሐ) <u>የታላቁ ባሕር አካባቢ አውራጃዎች</u>

1. ሉቅያ ከቶሩስ ተራራ በስተ ደቡብና በሩድ ደሴት ባሻገር ያለ አውራጃ ነበር ። ጳውሎስ በዚህ አውራጃ የነበሩትን ሁለት ከተሞች ፤ ጳጥራንና ሙራን ጐብኝቶአል ። (የሐዋ. ፳፩ ፥ ፩ ፤ ፳፯ ፥ ፭)

2. ኪልቅያ በቶሩስ ተራራና በታላቁ ባሕር መከከል የሚገኝ ሲሆን ዋናው ከተማ ጳውሎስ የተወለደበት ጠርሴስ ነበር ። (የሐዋ. ፱ ፥ ፲፩)

መ) <u>መአከላዊ አውራጃዎች</u>

1. ገላትያ የማህል አገር ከነበሩት አውራጃዎች በስተ ሰሜን የሚገኝ ነበር። ጳውሎስ ይህን አውራጃ ከመጐብኘቱም በላይ ለዚሁ አውራጃ ሕዝብ አንድ መልእክት ጽፎአል ። (የሐዋ. ፲፮ ፥ ፮ ፤ ፲፰ ፥ ፳፫ ፤ ገላ. ፩ ፥ ፪)


2. ቀጰዶቂያ ከገላትያ በስተ ምሥራቅና ከጳንጦስ በስተ ደቡብ ትገኝ ነበር። ከዚህ አገር ጥቂቶች ሰዎች በበዓለ ኀምሳ ዕለት በኢየሩሳሌም ነበሩ ። (የሐዋ. ፪ ፥ ፱)

3. ሊቃኦንያ (የሐዋ. ፲፬ ፥ ፮—፳፫) ኢቆንዮን ፥ ደርቤንና ፥ ልስጥራን የዚህ አውራጃ ከተሞች ነበሩ ። የሚገኙትም ከገላትያ በስተ ደቡብ ነበር ።

4. ጲስድያ በሊቃኦንያና በፍርግያ መከከል ይገኝ ነበር ። ዋና ከተማው አንጾኪያ ይባል ነበር ። ይህ ከተማ ከሶርያ አንጾኪያ የተለየ ሲሆን ፤ የሁለቱም ከተሞች ስም አንድ ነበር ። ጳውሎስ ይህን አውራጃ ጐብኝቶአል ። (የሐዋ. ፲፫ ፥ ፲፬ ፤ ፲፬ ፥ ፳፩—፳፪)

5. ፍርግያ ፥—ሎዶቅያና ቈላስይስ በዚህ አውራጃ የሚገኙ ከተሞች ነበሩ ።

## ፱ ፤ የመጀመሪያው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ
(የሐዋ. ፲፫ ፥ ፩—፲፬ ፥ ፳፰)


ጥቁር ባሕር
ተሰሎንቄ
ፍልጵስዩስ
ቤርያ
ጥሮአዳ
አቴና
ቆሮንቶስ
ኤፌሶን
አንጾኪያ
ኢቆንዮን
ልስጥራን
ደርቤን
ጰርግያ
የኤጂያን ባሕር
አንጾኪያ
ሴሌውቅያ
ስልማና
ጳፉስ
ታላቁ ባሕር
ቂሣርያ
ኢየሩሳሌም
የጳውሎስ
የመጀመሪያውና ሁለተኛው
የስብከት ጉዞ ።
፩ኛ የስብከት ጉዞ
፪ኛ የስብከት ጉዞ

ሀ) ጳውሎስ ፣ በርናባስና ዮሐንስ ማርቆስ ከሶርያው አንጾኪያ ተነሥተው ሄዱ ።

ለ) ከአንጾኪያ ፳፯ ኪሎሜትር ራቅ ብላ ትገኝ ወደ ነበረችው ወደ ሴሌውቆያ ሄዱ ።

ሐ) ከዚያም በመርከብ ወደ በርናባስ የጥንት መኖሪያ ወደ ቆጵሮስ ተሻገሩ ። ይህ ደሴት በታላቁ ባሕር ከትንሹ እስያ ደቡባዊ ጠረፍ ላይ ይገኛል ።

መ) በቆጵሮስ ምሥራቃዊ ጠረፍ በሰልማናም በነበሩ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ ።

ሠ) ወደ ምዕራብ በመጓዝ ደሴቲቱን አቋርጠው ወደ ዋና ከተማይቱ ወደ ጳፉስ መጡ ። በዚህች ከተማ ሰርግዮስ ጳውሎስ የተባለው አገረ ገዥ አመነ ።

ረ) ከዚህ ተነሥተው ወደ ሰሜን ምዕራብ ተጓዙና በትንሹ እስያ ወደምትገኘው ወደ ጵንፍልያ አውራጃ መጡ ። ጵርግያ ወደምትባለውም ከተማ ደረሱ ። እዚህ ዮሐንስ ማርቆስ ጳውሎስንና በርናባስን ትቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ ።

ሰ) ቀጥሎም ወደ ጲስድያው አንጾኪያ አመሩ ። ይህች ከተማ የምትገኘው ከኤፌሶን በስተ ምሥራቅና ከጠርሴስ በስተ ሰሜን ምዕራብ ነበር ። እዚያም አንድ ቤተ ክርስቲያን አቋቋሙ ።

ሸ) አይሁዶች በማሳደድ ስላስወጡአቸው ወደ ምሥራቅ ወደ ኢቆንዮን ከተማ ሄዱ ።

ቀ) እንደገናም በደረሰባቸው ሥቃይ ምክንያት ወደ ደቡብ ምሥራቅ ወደ ልስጥራን ተጓዙ ።

በ) ጳውሎስ በልስጥራን በድንጋይ ተደበደበ ። ከዚያም ተነሥና ወደ ደርቤን ሄደ ።

ተ) ከዚያም በቀላሉ በእግር መንገድ ወደ ጠርሴስና ወደ አንጾኪያ መሄድ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን በመጡበት መንገድ ተመልሰው እንደገና ልስጥራን፣ ኢቆንዮንና የጲስድያውን አንጾኪያ ጐበኙ ። ይህንንም ያደረጉት በእነዚህ ከተሞች የተቋቋሙትን አብያተ ክርስቲያናት ለማበረታታት ነበር ። ጵርግያ በደረሱ ጊዜ ወደ ኢጣልያ ወረዱ ። ከዚያም ወደ አንጾኪያ ተመለሱ ።

## ፫ ፣ ሁለተኛው የጳውሎስ የስብከት ጉዞ

(የሐዋ. ፲፭ ፣ ፴—፲፰ ፣ ፳፪)

በመጀመሪያውና በሁለተኛው የስብከት ጉዞዎቹ መከከል ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶአል (የሐዋ. ምዕራፍ ፲፭) ።

በዚህ በሁለተኛው ጉዞ ጳውሎስ በትንሹ እስያ ፣ በመቄዶንያና በግሪክ በኩል አድርጎ ሄደ ። በዚህ ጉዞ በዮሐንስ ማርቆስ የተነሣ ጳውሎስና በርናባስ አልተስማሙም ። ጳውሎስ ሲላስን ሲወስድ በርናባስ ደግሞ ማርቆስን ወስዶ ሁለቱም በልዩ ልዩ መንገዶች ሄዱ ።

ሀ) ጳውሎስ በእስያ የጐበኛቸው ቦታዎች

1· ሶርያ ፦ጳውሎስ ከአንጾኪያ ተነሥቶ በሶርያ በኩል አብያተ ክርስቲያናትን እየጐበኘ አለፈ (የሐዋ· ፲፭ ፥ ፵፩)። ከተሞቹ ግን አልተጠቀሱም።

2· ኪልቅያ ፦(የሐዋ· ፲፭ ፥ ፵፩) ወደ ተወለደበት አገር ወደ ጠርሴስ ሄደ።

3· ከጠርሴስ ተነሥቶ በመጀመሪያ ጉዞው ጐብኝቶት ወደ ነበረው ወደ ደርቤን ሄደ። (የሐዋ· ፲፮ ፥ ፩)

4· ከዚያ ቀጥሎ ያረፈው ለመጀመሪያ ጊዜ በጐበኘበት ወቅት በተደበደበበት በልስጥራ ነበር። ከዚህ ጢሞቴዎስ ተከተለው (የሐዋ· ፲፮ ፥ ፩—፬)

5· ቀጥሎም ወደ ፍርግያ ሄዱ።

6· ከፍርግያም ወደ ገላትያ ሄዱ።

7· ጢሮአዳ ፦ እዚህ ሉቃስ ጳውሎስን ተከተለና አብረው ሄዱ። ጳውሎስ ከመቄዶንያ አንድ ሰው እርዳታ ሲፈልግ በሕልሙ አየ። ምንም እንኳ ጳውሎስ ሊሄድ ያሰበበት መንገድ ቢኖረውም እግዚአብሔር ካሰበበት መንገድ አስቀርቶት በሌላ በኩል መራው። ከዚህም የተነሣ ወንጌል ወደ እስያ መድረሱ ቀርቶ ወደ አውሮፓ መጣ። (የሐዋ· ፲፮ ፥ ፮—፰)

ለ) ጳውሎስ በአውሮፓ የጐበኛቸው ቦታዎች

1· ፍልጵስዩስ (የሐዋ· ፲፮ ፥ ፲፪—፵) ፦እዚህ የመጀመሪያይቱ የአውሮፓ አማኝ የነበረችው ልድያ ተጠመቀች ፤ ቤተ ክርስቲያንም ተመሠረተ። ጳውሎስና ሲላስም በዚሁ ከተማ ውስጥ ተደብድበው ወደ ወኅኒ ገብተዋል። ነገር ግን የወኅኒው ጠባቂና ቤተ ሰቡ አምነው ተጠመቁ።

2· ተሰሎንቄ (የሐዋ· ፲፯ ፥ ፩—፱) ፦ይህ የመቄዶንያ ዋና ከተማ ነበር። በዚህ ከተማ ጳውሎስ በሦስት የሰንበት ዕለቶች ሰብከአል። እንደገና አይሁዶች ሊንድ ብለው ሊያሳድዱአቸው ስለ ተነሡ ከተማውን በሌሊት ለቅቆ መሄድ ግድ ሆነባቸው።

3· ቤርያ ፦የዚህ ከተማ ነዋሪዎች የጳውሎስን መልእክት እያዳመጡ ፤ ትክክለ ኛነቱንም ለማወቅ መጽሐፍ እየመረመሩ ስብከቱን ተከታተሉ። ከዚህም የተነሣ ጳውሎስ የሰበከው ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለውን ብቻ እንደ ነበር ለማስተዋል በመቻ ላቸው ብዙዎች አመኑ። (የሐዋ· ፲፯ ፥ ፲—፲፬)

4· አቴና (የሐዋ· ፲፯ ፥ ፲፭—፴፬) ፦ምንም እንኳ ጳውሎስ እዚህ ቢሰብክ ቤተ ክርስቲያን አልተቋቋመም።

5. ቆሮንቶስ (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፩—፲፰) ፡—ይህ ከተማ ከአቴና ወደ ምዕራብ 64 ኪሎሜትር የራቀ ነበር ። ጳውሎስ ድንኳን እየሰፋ አንድ ዓመት ከመንፈቅ በዚሁ ከተማ ሰብኮአል ። ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ሁለቱን መልእክት የጻፈው በዚሁ በቆሮንቶስ ከተማ ነበር ።

ሐ) <u>የጳውሎስ ወደ አንጾኪያ መመለስ</u>

1. ጳውሎስ የኤጂያንን ባሕር በማቋረጥ ወደ ምሥራቅ ከተጓዘ በኋላ ወደ ኤፌሶን ደረሰ ። (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፲፱—፳፩)

2. ከዚህም ተነሥቶ በትንሹ እስያ ደቡባዊ ምዕራብ ጠረፍ አድርጎ ወደ ቂሣርያ ሄደ ። (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፪)

3. ቀጥሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፪) ። በእዚያም ለነበሩት ምዕመናን ሰላምታ ለማቅረብ ትንሽ ከቈየ በኋላ ጕዞውን ቀጠለ ።

4. ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም መጀመሪያ ጕዞውን ወደ ጀመረበት ወደ ሶሪያው አንጾኪያ ሄደ ።

## ፬፤ ሦስተኛው የጳውሎስ የስብከት ጕዞ

(የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፫—፳፩ ፥ ፲፯) ።

ይህ ጕዞ ከ54—58 ዓ. ም. አራት ዓመት ወስዶአል ። ከዚህ ጊዜ ውስጥ ጳውሎስ ሦስቱን ዓመት በኤፌሶን አሳለፈ ።

ሀ) ወደ ምዕራብ መጓዝ (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፫—፳ ፥ ፫)


1. አንጾኪያ ፡—ጳውሎስ የወንጌልን ስብከት ጕዞዎቹን ሁሉ የጀመረው ከዚህ ነበር ።

2. ገላትያ ፡—(የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፫) ፡—ከዚህ ቀደም ባደረገው ጕዞ ያቋቋማቸውን አብያተ ክርስቲያናት ጐበኘ ።

3. ፍርግያ ፡—ጳውሎስ በስተ ምዕራብ በኩል በሚያደርገው ጕዞው ላይ እንደ ነበረ በዚህች አውራጃ በኩል አለፈ ። (የሐዋ. ፲፰ ፥ ፳፫)

4. ኤፌሶን ፡—(የሐዋ. ፲፱ ፥ ፩—፳ ፥ ፩) ፡—ይህች ከተማ ከኤጂያን ባሕር አንድ ኪሎሜትር ተኩል ራቅ የምትል ነበረች ። እዚህ ጳውሎስ ሦስት ዓመታት ያህል ቈይቶ አል ። ሰሞኑን ድንኳን እየሰፋ በሰንበት ዕለታት ደግሞ ወንጌልን ይሰብክ ነበር ። እዚህ ሳለ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የመጀመሪያውን መልእክቱን ጻፈ ።

5. ጥሮአዳ ፡—ጳውሎስ ወደ እዚህ ከተማ ያደረገው ጕዞ በሐዋርያት ሥራ አል ተጠቀሰም ። ይሁን እንጂ በ፪ ቆሮ. ፪ ፥ ፲፪ ፤ ፲፫ ይገኛል ።




ሦስተኛው የጳውሎስ
የስብከት ጉዞ ።

6· መቄዶንያ ፡—ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፳ ከቁጥር ፩—፪ እንደምናገኘው ጳውሎስ በመቄዶንያ በኩል ማለፉን እንጂ በተለይ የጐበኛቸውን ከተሞች ዝርዝር ለማወቅ አይቻልም ። ምናልባት ፊልጵስዩስን ፣ ተሰሎንቄንና ቤርያን ሳይጐበኝ አልቀረም የሚል አሳብ ለመሰንዘር ይቻል ይሆናል ። በመቄዶንያም ሳለ ፪ ቆሮንቶስን ጻፈ ።

7· ግሪክ (የሐዋ· ፳ ፡ ፪ ና ፫ ፤ ፲፰ ፡ ፳፯)፡—ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኑን ለማበረታታት ወደ ቆሮንቶስ ሄደ ። እዚያም በነበረበት ጊዜ ወደ ሮሜ ሰዎች አንድ መልእክት ጻፈ ። ወደ ገላትያም የጻፈው እዚሁ በነበረበት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም ።

ለ) የመልስ ጉዞ (የሐዋ· ፳ ፡ ፮—፳፩ ፡ ፲፯)

1· ፊልጵስዩስ ፡—ወደ እዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ወደ ጐበኘው ከተማ ሄደ (የሐዋ· ፳ ፡ ፫—፮)።

2· ጥሮአዳ ፡— ጳውሎስ ከሉቃስ ጋር ወደ ጥሮአዳ ሄዶ አንድ ሳምንት ተቀመጠ (የሐዋ· ፳ ፡ ፮—፲፫)። እዚያም በነበረበት ጊዜ አውጤኪስ የተባለውን ብላቴና ከሞት አዳነ ።

3· ሚጢሊኒ ፡—በዚህች ደሴት እምብዛም የተፈጸመ ነገር የለም ። (የሐዋ· ፳ ፡ ፲፬)

4· ሚሊጢን (የሐዋ· ፳ ፡ ፲፯—፴፰)፡—ከኤፌሶን በስተ ደቡብ ትገኝ ነበር ። በኤፌሶን የነበሩ ሽማግሎች ወደ እዚህ መጥተው ጳውሎስን ሲሄድ ተሰናበቱት ።

5· ሩድ (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፩)፡— ከትንሹ እስያ ጠረፍ ትንሽ ራቅ ብላ የምትገኝ ደሴት ነበረች ።

6· ጳጥራ (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፩)፡—በትንሹ እስያ በሉቅያ አውራጃ ውስጥ የባሕር ወደብ ነበረች ። ጳውሎስ የተጓዘበት መርከብ መድረሻ ይህችው ወደብ ስለ ነበረች አብረው ከነበሩት ጋር ሆኖ ወደ ፊንቄ በሌላ መርከብ ጉዞውን ቀጠለ ። (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፪)

7· ጢሮስ የፊንቄ ዋና ከተማ ነበር ። ጳውሎስ በዚህች ከተማ አንድ ቤተ ክርስቲያን ተቋቁሞ አገኘ ።

8· አካ ፡—ጳውሎስ በፍልስጥኤም ጠረፍ አድርጎ ወደ አካ በመርከብ ተጓዘ (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፯)። እዚያም ከደረሰ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ ምዕመናን ጋር አንድ ቀን ዋለ ።

9· ቂሣርያ (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፰)፡—ጳውሎስ ከአካ ተነሥቶ እዚህ አረፈ ። ምንም እንኳ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ቢያስጠነቅቁት ጳውሎስ ዝም ብሎ ሄደ (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፲—፲፫)። እዚያም በወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ተቀመጠ ።

10· ኢየሩሳሌም (የሐዋ· ፳፩ ፡ ፲፭)፡—ጳውሎስ ክርስቲያን ከሆነ ወዲህ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ ይህ አምስተኛውና የመጨረሻው ጊዜ ነበር ። ወዲያው ታስሮ ሄደ ።

# ፳፤ የጳውሎስ በእስረኛነት ወደ ሮሜ መሄድ

(የሐዋ· ፳፫ ፥ ፳፫—፳፰ ፥ ፴፩)።

ጳውሎስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሮሜ የሄደው ታስሮ ነበር ።

ሀ) ኢየሩሳሌም ፥—ታስሮ የሄደው ከዚህ ነበር ። (የሐዋ· ፳፫ ፥ ፴፩)

ለ) አንቲጳጥሪስ ፥—ወታደሮች በሌሊት ጳውሎስን እስከ እዚህ ድረስ አመጡት። (የሐዋ· ፳፫ ፥ ፴፩)

ሐ) ቂሣርያ (የሐዋ· ፳፫ ፥ ፴፫) ፥—እዚህ ጳውሎስ ሁለት ዓመታት ታሰረ። ጳውሎስ በሮማዊ ዜግነቱ በነበረው መብት መሠረት እንዲፈረድለት ለቄሣሩ ይግባኝ ስለ አለ ወደ ሮሜ ተላከ። (የሐዋ· ፳፯ ፥ ፩ ና ፪)

መ) ሲዶና ፥—ጳውሎስ እርዳታቸውን ይቀበል ዘንድ ወደ ወዳጆቹ እንዲሄድ ተፈቀደለት። (የሐዋ· ፳፯ ፥ ፫)

ሠ) ሙራ (የሐዋ· ፳፯ ፥ ፬—፮) ፥—እዚህ ከደረሱ በኋላ ጳውሎስን ወደ ላሌ መርከብ አሳፈሩት ።

ረ) ቀርጤስ ፥—ነፋሱ ወደ ኋላ ስለ ነፈሰባቸው በቀርጤስ ደሴት ላይ አረፉ። ይህችም ደሴት ከግሪክ አገር በስተ ደቡብ ምሥራቅ ትገኝ ነበር። ምንም እንኳ ከዚህ እንዳይነሡ ጳውሎስ ቢያስጠነቅቃቸው ዝም ብለው የባሕር ላይ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ግን ጳውሎስ እንደተናገረው ችግር ደረሰባቸው። (የሐዋ· ፳፯ ፥ ፯—፲፫)

ሰ) መላጥያ (የሐዋ· ፳፰ ፥ ፩—፲፩) ፥—ከቀርጤስ እንደ ተነሡ ማዕበል መጣባቸው። ነፋሱ አሥራ አራት ቀንና ሌሊት ወደ ምዕራብ ነዳቸው። በመጨረሻም ወደ መላጥያ ደሴት መጡ። መላጥያ ከሲሲሊ ደሴት 100 ኪሎሜትር ያህል ወደ ደቡብ ይርቃል። እዚህ ጳውሎስ የደሴቱን አለቃ አባት ፈወሰ።

ሸ) ከክረምት በኋላ ጉዞአቸውን ቀጥለው በሲሲሊ ምሥራቃዊ ጠረፍ ላይ በሰራኩስ ከተማ አረፉ (የሐዋ· ፳፰ ፥ ፲፪)። ከዚያም ለሦስት ቀናት ቈዩ።

ቀ) ከሰራኩስ ከተማ ከተነሡ በኋላ ያረፉት በሬጊዩም ነበር (የሐዋ· ፳፰ ፥ ፲፫)። ይህ ከተማ በኢጣሊያ ደቡባዊ ጫፍ ላይ ነበር።

በ) ቀጥሎም ወደ ፑቲዮሉስ መጡና አንድ ሳምንት ተቀመጡ። (የሐዋ· ፳፰፡ ፲፫ ና ፲፬)

ተ) ከዚያም በ አፍዩስ ፋሩስ ገበያና "በሦስት ማደሪያ" አድርገው ጉዞአቸውን ወደ ሮሜ ቀጠሉ። (የሐዋ· ፳፰ ፥ ፲፭)

ቸ) ሮሜ የተመሠረተችው በጣይበር ወንዝ ዳርቻ ሲሆን የተከተመችው ግን በአ ሥር ኮረብታዎች ላይ ነበር። ጳውሎስ ታስሮ በነበረበት ጊዜ የዚህች ከተማ ነዋሪዎች ብዛት ወደ 1,200,000 ይገመት ነበር። ከእነዚሁም እኩሌታዎቹ በባርነት የሚሠቃዩ ሲሆኑ ከቀሩት ደግሞ አብዛኞቹ ድህነት ያጠቃቸው ነበሩ።

ጳውሎስ እዚህ ሲደርስ ጉዞውን አበቃ። በዚህች ከተማ ለሁለት ዓመታት በእስረ ኛነት ሲቆይ በዘበኛ እየተጠበቀ ቤት ተከራይቶ እንዲቀመጥ ተፈቀደለት (የሐዋ. ፳፰ ፥፲፮ ና ፴—፴፩)። እርሱም ይሰብክና ያስተምር ስለ ነበረ ከቄሣሩ ቤተ ሰብ አንዳንዶቹ ፤ እንዲ ሁም ብዙ ሰዎች ሊያምኑ ቻሉ። (ፊልጵ. ፩ ፥ ፳፩)

ጳውሎስ እስረኛ በነበረበት ጊዜ የሚከተሉትን መልእክቶች ጽፎአል ፦

1. ወደ ኤፌሶን ሰዎች

2. ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

3. ወደ ቈላስያስ ሰዎች

4. ወደ ፊልሞና

ለሁለት ዓመታት ከታሰረ በኋላ ጳውሎስ ለጊዜው ተለቆ ነበር። በዚህም ጊዜ ፩ ጢሞቴዎስን ጻፈ። ዳግመኛ በታሰረም ጊዜ ፪ ጢሞቴዎስን ጽፎአል። ይህም የመጨ ረሻው መልእክት ነበር።

## ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት

በእስያ የነበሩት ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በዮሐንስ ራእይ ከምዕራፍ ፪ እስከ ፫ ተጠቅሰዋል። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተበት ከተማ ስም የታወቀ ነበር። ይህም ምዕራፍ ስለ ሰባቱ ከተሞችና ሐዋርያው ዮሐንስ የራእዩን መጽሐፍ በጻፈ ጊዜ ስለተቀመጠበት ደሴት ስለ ፍጥሞ ባጭሩ ይገልጻል።

1. ኤፌሶን (፪ ፥ ፩) ከእነዚህ ከተሞች ሁሉ በይበልጥ የታወቀች ስትሆን ቤተ ክርስቲያኑም ከሁሉ ይበልጥ ነበር።

2. ሰምርኔስ (፪ ፥ ፰) ከኤፌሶን 64 ኪሎሜትር ወደ ሰሜን ራቅ ብሎ በኤጂያን ባሕር ዳር ይገኝ ነበር ፤ ዛሬም ሰፊ ከተማ ነው።

3. ጴርጋሞን (፪ ፥ ፲፪) ከሰምርኔስ 96 ኪሎሜትር ወደ ሰሜን ምሥራቅ ፥ ከኤ ጂያን ባሕር ደግሞ 32 ኪሎሜትር ራቅ ብሎ ይገኝ ነበር።

4. ትያጥሮን (፪ ፥ ፲፫) በልድያ አውራጃ ከጴርጋሞን በስተ ደቡብ ምሥራቅ ይገኝ ነበር።


5· ሰርዴስ (፫ ፡ ፩) ከትያጥሮን 48 ኪሎሜትር በስተ ደቡብ ነበር ።

6· ፊልድልፍያ (፫ ፡ ፯) ከሰርዴስ 40 ኪሎሜትር በስተ ደቡብ ምሥራቅ ነበር ።

7· ሎዶቅያ (፫ ፡ ፲፬) የፊርግያ ዋና ከተማ ሲሆን ከፊልድልፍያ 88 ኪሎሜትር ያህል ራቅ ይል ነበር ።

<u>ፍጥሞ</u> (፩ ፡ ፱)

ከኤፌሶን በስተ ደቡብ ምዕራብ በኤጂያን ባሕር ትገኝ ነበረች ። ይህች ደሴት ድንጋያማና ደረቅ አገር ነበረች ። ሐዋርያው ዮሐንስ በስተ እርጅና ወደ እዚህች አገር ተሰድዶአል ። ራእዩንም የጻፈው እዚሁ ነበር ።




የጳውሎስ ወደ ሮሜ ጉዞና ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ።


5. ሰርዴስ (፫ ፡ ፩) ከትያጥሮን 48 ኪሎሜትር በስተ ደቡብ ነበር ።

6. ፊልድልፍያ (፫ ፡ ፯) ከሰርዴስ 40 ኪሎሜትር በስተ ደቡብ ምሥራቅ ነበር ።

7. ሎዶቅያ (፫ ፡ ፲፬) የፊርግያ ዋና ከተማ ሲሆን ከፊልድልፍያ 88 ኪሎሜትር ያህል ራቅ ይል ነበር ።

<u>ፍጥሞ</u> (፩ ፡ ፱)

ከኤፌሶን በስተ ደቡብ ምዕራብ በኤጂያን ባሕር ትገኝ ነበረች ። ይህች ደሴት ድንጋያማና ደረቅ አገር ነበረች ። ሐዋርያው ዮሐንስ በስተ እርጅና ወደ እዚህች አገር ተሰድዶአል ። ራእዩንም የጻፈው እዚሁ ነበር ።




የጳውሎስ ወደ ሮሜ ጉዞና ሰባቱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ።